ኣብ ግዚያዊ ምምሕዳር ትግራይ
THE INTERIM REGIONAL ADMINISTRATION OF TIGRAY
ቤት ፅሕፈት ፕሬዚደንት
OFFICE OF THE PRESIDENT

ዕለት
Date 28/3/2016

ቑፅሪ
Ref.No 91/27/8/04

ናብ ቢሮ ፍትሒ ክልል ትግራይ

<u>መቐለ</u>

**ዋኒኑ፦ <u>መሰጋገሪ ደንቢ ቑፅሪ 4/2016 ዓ/ም ምልኣኽ ይምልከት</u>**

ኣብ ርእሲ ዋኒን ከም ዝተገለፀ ብቢሮ ፍትሒ ዝቐረበ <u>ካብ ሕግታት ህዉሶ እዋን ናብ ስሩዕ ሕጊ ንምምላስ</u> ዝወፀ መሰጋገሪ ረቒቕ ደንቢ ናብ ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ቐሪቡ እዩ ::

በቲ ዝቐረበ ዝርዝር መሰረት <u>ቤት ምኽሪ ካቢኔ ግዚያዊ ምምሕዳር ትግራይ ብዕለት 26/03/2016 ዓ/ም ኣብ ዘካየዶ ስሩዕ ኣኼባኡ</u> በቲ ዝቐረበሉ ዝርዝር ዘተ ብምግባር 14 ዓንቀፃትን 12 ገፅን ዝሓዘ <u>ካብ ሕግታት ህዉሶ እዋን ናብ ስሩዕ ሕጊ ንምምላስ</u> ዝወፀ ካብ ሕግታት ህዉሶ እዋን ናብ ስሩዕ ሕጊ ንምምላስ መሰጋገሪ ደንቢ ኣፅዲቑ ስለ ዘሎ እዚ ደንቢ ካብ ዝፀደቐሉ ዕለት ጀሚሩ ዝምልከተኩም ኣካላት ኩሉኹም ኣብ ስራሕ ክተውዕልዎ የተሓሳስብ ::

ምስ ሰላምታ

Getachew

ጌታቸው ረዳ ካሕሳይ
ፕሬዚደንት ግዚያዊ ምምሕዳር ትግራይ

<u>ቅዳሕ</u>

- ✓ ንካ/ሲ/ስ/ምም/ዴሞክራታይዘሽን
- ✓ <u>ንላዕለዋይ ቤት ፍርዲ</u>

<u>መቐለ</u>

0996402421



17.1.16

Scanned with AnyScanner

## ቁፅሪ ደንቢ 4/2010 ዓ/ም

## ካብ ሕግታት ህፁፅ እዋን ናብ ስሩዕ ሕጊ ንምምላስ ዝወፀ መሰጋገሪ ደንቢ

ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ብምጥሓስ ኣብ ልዕሊ ህዝቢ ትግራይ ዘርኣዊ ምፅናት ዝኸደ ብልዕንቱ ስለዝተኻየደን እዚ ንምምካት ብመላእ ትግራይ ኣድላዪ ስጉምቲ እናተወሰደ ስለዝነበረ፤

ኣብ ደቡብ ኣፍሪካ ዝተፈረመ ሰላም ንምስፋንን ተኹሲ ብዘላቒነት ደው ንምባል ውዕሊ ሰላም ፕሪቶሪያ ብምኽታም መረፃ ንምክያድ ጥዑም ኩነታት ዝፈጥር ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ስለዝተጣየሸ፤

ናብ ስሩዕ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ንምምላስን ውዕሊ ሰላም ፕሪቶሪያ ንምትግባርን ክሕግዝ ዝኽእል ስጉምቲ ምውሳድ ኣድላዪ ምዃኑ ስለዝተኣመነሉ፤

ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ብመሰረት ዓንቀፅ 15 (1) ቁፅሪ ኣዋጅ 359/1995 ዓ/ምን ቤት ምኽሪ ሚኒስተራት ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ንምጥያሽ ዝወፀ ቁፅሪ ደንቢ 533/2015 ዓ/ም ዓንቀፅ 5 (1)ን ዝተውሃቦ ስልጣን እዚ ደንቢ ኣውፂኡ ኣሎ።

## ደንብ ቁጥር 4/2010 ዓ/ም

## ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ህጎች ወደ መደበኛ ህግ ለመመለስ የወጣ የመሸጋገሪያ ደንብ

በትግራይ ህዝብ ላይ ህገ መንግስታዊ ስርዓት በመጣስ የዘር ማጥፋት ወንጀል በማስፈፀም ስለተካሄደ እና ይህንን ለመመከት በትግራይ በሙሉ አስፈላጊ እርምጃ እየተወሰደ በመሆኑ፤

በደቡብ አፍሪካ በተፈረመ ሰላም ለማስፈን እና ግጭት በዘላቂነት ለማቆም የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት በመፈረም ምርጫ ለማካሄድ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ስለተቋቋመ፤

ወደ መደበኛ ህገ መንግስታዊ ስርዓት መመለስ እና የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ማስፈጸም ሊያግዝ የሚችል እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር በአዋጅ ቁጥር 359/1995 ዓ/ም አንቀጽ 15 (1) እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 533/2015 ዓ/ም አንቀጽ 5 (1) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

Scanned with AnyScanner

## ክፋል ሓደ
## ሓፈሻዊ ድንጋገ

### ዓንቀፅ 1. ሓጺር ርእሲ

እዚ ደንቢ "ናብ ስሩዕ ሕጊ ንምምላስ ዝወፀ ቁፅሪ ደንቢ 4/2016 ዓ/ም" ተባሂሉ ክጥቀስ ይኽእል።

### ዓንቀፅ 2. ትርጉም

ኣብዚ ደንቢ፦

1. "ክልል" ማለት ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ፤
2. "ምምሕዳር" ማለት ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ እዩ፤
3. "ርእሰ ምምሕዳር" ማለት ርእሰ ምምሕዳር ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ'ዩ፤
4. "ቤት ምኽሪ ሰላም ፀጥታን" ማለት ሰላም፣ ፀጥታን ድሕንነትን ክልል ዘረጋግፅ ብርእሰ ምምሕዳር ዝውደብን ዝምራሕን ንልእኹ ኣድለይቲ ዝኾኑ ሰባት ዝሓዘ ቤት ምኽሪ እዩ፤
5. "ኣካላት ፀጥታ" ማለት ኣብ ትሕቲ ክቢ ሲክሬታርያት ሰላምን ፀጥታን ተወዲቦም ዝርከቡ ኣካላት ፀጥታ ዘካትት ይኾኑ፤
6. "ስሩዕ ሕጊ" ማለት ብመሰረት ሕገመንግስቲ ፈደራል መንግስቲ

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ወደ መደበኛ ህጊ ለመመለስ የወጣ ደንብ ቁጥር 4/2016 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2. ትርጉም

በዚህ ደንብ፦

1. "ክልል" ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነው፤
2. "አስተዳደር" ማለት የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ነው፤
3. "ርዕሰ መስተዳድር" ማለት የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርዕሰ መስተዳድር ነው፤
4. "የሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት" ማለት የክልሉ ሰላም፣ ፀጥታና ደህንነት የሚያረጋግጥ በርዕሰ መስተዳድሩ የሚደራጅና የሚመራ ለተልእኮው አስፈላጊ የሆኑ ሰዎች የያዘ ምክር ቤት ነው፤
5. "የጸጥታ አካል" ማለት በሰላምና ፀጥታ ሴክሬታርያት ስር ተደራጅተው የሚገኙ የፀጥታ አካላት ያካተተ ይሆናል፤
6. "መደበኛ ህግ" ማለት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት መሰረት የፌዴራል

Scanned with AnyScanner

ፌደራልን ክልልን ኣብ ሕጋዊ ስልጣኖም ኮይኖም ዘውፅእዎም መሰረታውን ስነ ስርዓታውን ሕግታትዮም።

7. "ኣዋጃት ህፁፅ እዋን" ማለት ቁፅሪ ኣዋጅ 358/2014 ዓ/ምን ዝተመሓየሸ ኣዋጅ ቁፅሪ 359/2014 ዓ/ም ኩነታት ህፁፅ እዋን ትግራይን ካብ ኩናት ናብ ሰላም ንምስግጋርን ድሕንነት ህዝቢ ትግራይ ንምሕላውን ዝወፅአ ቁፅሪ ኣዋጅ 365/2015 ዓ/ም ካልኦት ካብ ስሩዕ ሕግታት ወፃኢ ኣብ ህፁፅ እዋን ወፂኦም ኣብ ስራሕ ዝወዓሉ ኣዋጃትን እዮም።

8. "ደንብታት ህፁፅ እዋን" ማለት ኣብ ትግራይ ዝወፅኡ ቁፅሪ ደ.ን.ቢ. 115/2014 ዓ/ም፣ ቁፅሪ ደ.ን.ቢ. 117/2014፣ ቁፅሪ ደ.ን.ቢ. 118/2014 ዓ/ም፣ ቁፅሪ ደ.ን.ቢ.119/2014 ዓ/ም ቁፅሪ ደ.ን.ቢ. 120/2014ን ካልኦት ካብ ስሩዕ ሕግታት ወፃኢ ኣብ ህፁፅ እዋን ወፂኦም ኣብ ስራሕ ዝወዓሉ ደንብታትን እዮም።

9. "ሰብ" ማለት ተፈጥሮኣዊ ሰብ ወይ ብሕጊ መሰል ሰብነት ዝተውሃቦ ኣካል እዩ።

መንግስት እና ክልል በህጋዊ ስልጣናቸው ላይ ሆነው ያወጧቸው መሰረታዊ እና ስነ ስርአታዊ ህጎች ነው።

7. "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች" ማለት የትግራይ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ አዋጅ ቁጥር 358/2014 ዓ.ም እና የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 359/2014 ዓ/ም እንዲሁም ከጦርነት ወደ ሰላም ለመሸጋገር እና የትግራይ ህዝብ ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 365/2015 ዓ/ም እና ሌሎች ከመደበኛ ህጎች ውጪ ሆነው የአስቸኳይ ጊዜ ወጥተው በስራላይ የዋሉ አዋጆች ናቸው።

8. "የአስቸኳይ ጊዜ ደንቦች" ማለት በትግራይ የወጡ ደንብ ቁጥር 115/2014 ዓ/ም፣ ደንብ ቁጥር 117/2014 ዓ/ም፣ ደንብ ቁጥር 119/2014 ዓ/ም፣ ደንብ ቁጥር 120/2014 ዓ/ም እና ሌሎች ከመደበኛ ህጎች ውጪ ሆነው የአስቸኳይ ጊዜ ወጥተው በስራላይ የዋሉ ደንቦች ናቸው።

9. "ሰብ" ማለት ተፈጥሯዊ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

Scanned with AnyScanner

ዓንቀፅ 3. ኣገላልፃ ፆታ

ኣብዚ ደንቢ ብተባዕታይ ፆታ ዝተገለፀ ንኣንስታይ ፆታ'ውን ይገልፅ'ዩ።

*ዓንቀፅ 4. ወሰን ተፈፃምነት

እዚ ደንቢ ኣብ ክልልን ኣብ ክልል ዝነብር* ዝኾነ ሰብን ተፈፃሚ ይኸውን።

## ክፋል ክልተ

## ምጥያሽ፣ ስልጣንን ተግባርን ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን

ዓንቀፅ 5. ምጥያሽ

1. ከም ኣገባብነቱ ነዚ ደንቢ ዘፈፅምን ሰላም፣ ፀጥታን ድሕንነትን ክልል ዘረጋግፅ ብርእሰ ምምሕዳር ዝውደብን ዝምራሕን ንልእኹ ኣድለይቲ ዝኾኑ ሰባት ዝሓዘ ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን በዚ ደንቢ ተጣይሹ ኣሎ፣
2. በዝሒን ተዋፅኦን ኣባላት ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን ብርእሰ ምምሕዳር ይውሰን፣

ዓንቀፅ 6. ስልጣንን ተግባርን ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን

1. ምስ ውዕሊ ሰላም ፕሪቶሪያ ብዝተኣሳሰረ ሰላም ብዝበለፀ ክሰምርን ናብ ዝሓሸ መድረኽ

አንቀጽ 3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይገልጻል።

አንቀጽ 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በክልል እና በክልሉ በሚኖር ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## የሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት መቋቋም፣ ስልጣንና ተግባር

አንቀጽ 5. መቋቋም

1. እንደ አግባብነቱ ይህንን ደንብ የሚያስፈጽም እና የክልሉ ሰላም፣ ጸጥታ እና ደህንነት የሚያረጋግጥ በርዕሰ መስተዳድር የሚደራጅ እና የሚመራ ለተልእኮው አስፈላጊ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩት የሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፣
2. የሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት አባላት ቁጥር እና ተዋጽኦ በርዕሰ መስተዳድር ይወሰናል፣

አንቀጽ 6. የሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. ከፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ጋር በተያያዘ ሰላም ይበልጥ ስር እንዲሰድ እና ወደ ተሻለ መድረክ እንዲሸጋገር



Scanned with AnyScanner

ክሲ.ጋገር ንምግባር ዝኸእል ስትራተጂን ሕግታትን ንምውጻእ ዝኽእል ሓሳብ የቕርብ፣ እንትፀድቕ ኣብ ተግባር የውዕል፣

2. ሰላም ንምሕላውን ፀጥታ ንምኽባርን ኣገባብነት ምስ ዘለዎም ኣካላት ብምትሕብባር ይሰርሕ፣ ሰላም ክሰፍን ዝኽእል መደላ ይሕንፅፅ፣ ስራሕቲ ጥንቃቐ ይፍፅም፣
3. ዝተፈረመ ውዕል ሰላም ፕሮቶኮል ብመሉእነት ክሳብ ዝፍፀም ሰላምን ድሕንነትን ህዝቢ ትግራይ ክሳብ ዝምለስን *ንኹሉም ኣካላት ፀጥታ ይውድብ፣ ይመርሕ፣ ስልጣንን ተግባርምን ይውስን፣ ዝርዝሩ ብቤት ምኽሪ ፈፃሚ ስራሕ ግዚያዊ መንግስቲ ትግራይ ብዝውፅእ ደንቢ ይውሰን፣
4. ንሰላም ህዝብን መንግስትን ትግራይ ሓደጋ ዝኾነ ፍልፍል *ስግኣታት ብምፍላይ ክውሰድ ዝግብኦ ስጉምቲ ፈልዩ ይውስን፣ ብርእሲ ምምሕዳር እንተሕዘዝ ስጉምቲ ይወስድ፣
5. ሓፈሻዊ ቀመናን ህንፀትን ኣካላት ፀጥታ ትግራይ ዝምልከት ውሳኔታት የሕልፍ፣ ስትራተጂታትን ኣተገባብርኡን ትልሚ የፅድቕ፣ ንሰላምን ድሕንነትን ህዝቢ ትግራይ ዝድሊ ኣወዳድባ

ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂ እና ህጎች ለማውጣት የሚያስችል ሃሳብ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ተግባር ላይ ያውላል፣

2. ሰላም ለመጠበቅ እና ጸጥታ ለማስከበር አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣ ሰላም ለማስፈን የሚያስችል ዘዴ ይነድፋል፣ የጥንቃቄ ስራዎች ይፈጽማል፣
3. የተፈረመው የፕሮቶኮል የሰላም ስምምነት ሙሉ በሙሉ እስከሚፈጸም እና የትግራይ ህዝብ ሰላም እና ደህንነት እስኪመለስ ድረስ ለሁሉም የትግራይ ክልል የጸጥታ አካላት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ስልጣንና ተግባራቸው ይወስናል ዝርዝሩ የትግራይ ክልል ግዚያዊ አስተዳደር ስራ አስፈጻሚ ምክርቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፣
4. ለትግራይ ህዝብ እና መንግስት የሰላም አደጋ የሆኑ የስጋት ምንጮች በመለየት ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ለይቶ ይወስናል፣ በርዕሰ መስተዳድር ሲታዘዝ እርምጃ ይወስዳል፣
5. አጠቃላይ የትግራይ የጸጥታ አካላት ቁመና እና ግንባታ በተመለከተ ውሳኔዎች ያሳልፋል፣ ስትራቴጂዎች እና አተገባበሩ እቅድ ያጸድቃል፣



Scanned with AnyScanner

ይወስን፣

6. ኣብ መላእ ትግራይ ሓይሊ ፀጥታ ብምውፋር ሰላምን ፀጥታን ክኽበሩ፣ ካብ ሕጊ ወፃኢ ዝተዓጠቑ ኣካላት ዕጥቆም ክፍትሑ፣ ኩሉ ከባቢታት ብምቁፃፃር ሰላማዊ ናብራ ህዝቢ ክቕፅል ክሰርሑ ትእዛዝ ክህብ ይኽእል፣
7. ንሰላምን ፀጥታን ህዝብን መንግስትን ትግራይ ኣብ ስግኣት ዘውድቕ ወይ ከውድቕ ዝኽእል ኩነታት እንተጋጢሙ ብርእሲ ምምሕዳር እንትእዘዝ ኣድላዪ ውሳኔን ስጉምትን ክወስድ ይኽእል፣
8. ኣባላትን ኣመራርሓን ኣካላት ፀጥታ ስራሖምን ሓላፍነቶምን ኣብ ምውፃእ ዝፍጠር ተሓታትነት ገበን ብዝምልከት ዝርዝሩ ብዝወፅእ ደንቢ ይውሰን።

ዓንቀፅ 7. ስርዓት ኣኼባ

1. ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን ብርእሲ ምምሕዳር እንትፅዋዕ ኣብ ዝኾነ እዋን ክእከብ ይኽእል፣
2. ካብ መንጎ ኣባላት ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን ልዕሊ ፍርቂ እንተተረኺቦም ምልኣተ ጉባኤ ይኸውን፣
3. ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን ትግራይ

ለትግራይ ህዝብ ሰላም እና ደህንነት የሚያስፈልግ አደረጃጀት ይወስናል፤

6. በመላው የትግራይ ክልል የጸጥታ ሃይል በማሰማራት ሰላም እና ጸጥታ እንዲያከብሩ፤ ከህግ ውጭ የታጠቁ አካላት ትጥቅ እንዲፈቱ፤ ሁሉም አከባቢዎች በመቆጣጠር ሰላማዊ የህዝብ ኑሮ እንዲቀጥል እንዲሰሩ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፤
7. አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ወንጀል በመፈጸም፣ በመመከር ወይም በመዘጋጀት ላይ ተሳትፏል ተብሎ የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም በመደበኛ ህግ ተጠያቂ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፤
8. የፀጥታ አካላት አባሎችና አመራሮች ስራና ሃላፊነታቸው በሚወጡበት የሚፈጠር የወንጀል ተጠያቂነት በሚመለከት ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

አንቀጽ 7. የስብሰባ ስነ ስርአት

1. የሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት በርዕሰ መስተዳድር ሲጠራ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. ከሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤
3. የትግራይ የሰላም እና ጸጥታ ምክር



Scanned with AnyScanner

ናይ ባዕሉ መምርሒ ስነ-ስርዓት ኣኼባ ክህልዎ ይኽእል።

ዓንቀፅ 8. ምጥያሽ ንኡስ ቤት ምኽሪ

1. ጉባኤ ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን ዝሕግዙ ንኡሳን ኣባይቲ ምኽሪ ክጣየሽ ይኽእል፤
2. ቤት ምኽሪ ሰላምን ፀጥታን ስልጣንን ተግባርን ከምኡ'ውን ብዝሒ ኣባላት ሕድ ሕድ ንኡስ ቤት ምኽሪ ብመሰረት ዘውፅኦ መምርሒ ይውሰን።

ክፋል ሰለስተ

ናብ ስሩዕ ሕጊ መሰጋገሪ ድንጋገታት

* ዓንቀፅ 9. ተፈፃምነት ስሩዕ ሕጊ

1. እዚ ድንቢ ካብ ዝፀደቐሉ ዕለት ጀሚሩ ስሩዕ ሕጊ ተፈፃምነት ይህልዎ፤
2. እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተጠቐሰ እንተሃለወ እውን ብመሰረት ሕግታት ህፁፅ እዋን ትግራይ ኣብ ቤት ፍርዲ ኣብ ከይዲ ክሲ ወይ ይግባኣኒ ዝርከብ ዋኒን ወይ መዝገብ ዝኾነ ፍታብሄርን ብዝተኸሰሰሉ ሕግታትን ስነ ስርዓት ሕግታትን

* Subject to Political Negotiation

ቤት የራሱ የስብሰባ መመሪያ ሊኖረው ይችላል።

አንቀጽ 8. የንኡስ ምክር ቤት መቋቋም

1. ለሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት የሚያግዙ ንኡሳን ምክር ቤቶች ሊቋቋሙ ይችላሉ፤
2. የሰላም እና ጸጥታ ምክር ቤት የእያንዳንዱ ንኡስ ምክር ቤት አባላት ቁጥር እና ስልጣንና ተግባር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል።

ክፍል ሦስት

ወደ መደበኛ ህግ መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 9. መደበኛ ህግ ስለመፈጸም

1. ይህ ደንብ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ መደበኛ ህግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰ ቢኖርም በአስቸኳይ ጊዜ ህጎች መሰረት በፍርድ ቤት በክስ ወይም ይግባኝ በሂደት የሚገኝ የወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳይ ወይም መዝገብ በተከሰሰበት የአስቸኳይ ጊዜ ህግና የስነ ስርዓት ህግ መሰረት ቀጥሎ ዕልባት የሚያገኝ ይሆናል፤



Scanned with AnyScanner

ህፁፅ እዋን መሰረት ቀዋሚ መዕለቢ ዝረኽብ ይኸውን፤

3. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝተወሰነ ዋኒን ገበን ወይ ፍታብሄር ዝሰዓል ሕቶ ይግባኣኒ ብመሰረት ብዝተኸሰሰሉ ሕግታትን ስነ ስርዓት ሕግታትን ህፁፅ እዋን መሰረት ቀዋሚ መዕለቢ ዝረኽብ ይኸውን።

* ዓንቀፅ 10. ይግባኣኒ

1. ዝኾነ ሰብ ብይግባኣኒ ክርአ ዝግበኦ ዋኒን እንተልዩዎ ናብ ስልጣን ዘለዎ ኣካል ፀይቱ ይግባኣኒ ክሓትት መሰሉ ዝተሓለወ እዩ፤
2. ድንጋገ ንኡስ ዓንቀፅ 1 እዚ ዓንቀፅ እንተሃለወውን ኣብ ህፁፅ እዋን ብመሰረት ሕግታት ህፁፅ እዋን መዕለቢ ዝረኸበ ዋኒናት ገበንን ፍታብሄርን ሕቶ ይግባኣኒ ፌደራል ስበር ዝምልከት ጉዳያት ምምሕዳር ክልል ትግራይን መንግስቲ ፌደራልን ብሓበር ብዝወሰንዎ ሕጊ ወይ መምርሒ ክሳብ ዝወፅእ ተኣጊዱ ዝፀንሕ ይኸውን።

* Subject to Political negotiation?

3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት የተወሰነ የወንጀል ወይም ፍታብሄር ጉዳይ ላይ የሚነሳ የይግባኝ ጥያቄ በተከሰሰበት የአስቸኳይ ጊዜ ህግና የስነ ስርዓት ህግ መሰረት ቋሚ ዕልባት የሚያገኝ ይሆናል።

አንቀጽ 10. ይግባኝ

1. ማንኛውም ሰው በይግባኝ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ካለው ስልጣን ባለው የዳኝነት አካል ይግባኝ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው፤
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም በአስቸኳይ ጊዜ ወቅት በአስቸኳይ ጊዜ ህጎች መሰረት እልባት ያገኙ የወንጀልና የፍታብሄር ጉዳዮች የፌደራል ሰበር ይግባኝ የሚመለከት ጥያቄ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር እና የፌደራል መንግስት በጋራ በሚያወጡት ህግ ወይም መመሪያ እስከሚወሰን ድረስ ታግዶ የሚቆይ ይሆናል።

Scanned with AnyScanner

## ክፋል ሰለስተ

## ዝተፈላለዩ ድንጋገታት

### ዓንቀፅ 11. መሰጋገሪ

1. ኣዋጅ ህፁፅ እዋን ትግራይ መሰረት ገይሩ ዝወፀ መምርሒ ኣፈፃፅማ ክፍሊት ግዛ ክራይ ብግልፂ ክሳብ ዝስዓር ተፈፃምነት ይህልዎ፣
2. ቑፅሪ ኣዋጅ 360/2014 ዓ/ም ከሚሽን ፖሊስ መንግስቲ ትግራይ ዳግም ንምጥያሽ፣ ስልጣኑን ተግባሩን ንምውሳን ዝወፀ ኣዋጅ ምስ ስሩዕ ሕግታት ተመዛዚኑ ክሳብ ዝመሓየሽ ተፈፃምነት ይህልዎ፣
3. ካብ ጥቅምቲ 24/2013 ዓ/ም ክሳብ ሕዳር 30/2015 ዓ/ም ዘሎ ሕቶ ጠዝፍ መሃያ ሰራሕተኛታት መንግስቲ፣ ሰራሕተኛታት ውልቃ ትካላትን ሰራሕተኛታት ውልቀ ሰብን ዝምልከት ሓዱሽ ዋኒን ክሲ ምትእንጋድ ተኣጊዱ ይፀንሕ፡፡ ብተመሳሳሊ ኣብ ክይዲ ክሲ፣ ይግበኣኒን ኣፈፃፅማን ዝርከቡ ዋኒናት ክሳብ ዝምልከቶም ኣካላት መንግስቲ ተፀኒዑ መፍትሒ ዝግበረሉ ኣብ ዘለውዎ ደው ኢሎም ይፀንሑ፣
4. ንኣፈፃፅማ እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 3 ዝተገለፀ ፅንዓት ኣብ ውሽጢ ሽዱሽተ ወርሒ ክካየድ ኣለዎ፣ ኣብዚ

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 11. መሸጋገሪያ

1. የትግራይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መሰረት በማድረግ የወጣው የቤት ኪራይ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ በግልጽ እስኪሻር ድረስ ተፈጻሚነት ይኖሮዋል፤
2. የትግራይ ፖሊስ እንደገና ለማደራጀትና ስልጣኑና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 360/2014 ዓ/ም ከመደበኛ ህጎች ተመዛዝኖ እስከሚሻሻል ተፈፃሚነት ይኖረዋል፣
3. ከጥቅምት 24/2013 ዓ/ም እስከ ህዳር 30/2015 ዓ/ም ያለ የመንግስት ሰራተኛ፣ የግል ተቋማት ሰራተኛና የግለ ሰው ሰራተኛ ውዝፍ ደሞዝ የሚመለከት አዲስ የክስ ጉዳይ ታግዶ ይቆያል፡፡ በተመሳሳይ በሂደት ላይ ያሉ ክስ፣ ይግባኝና አፈፃፀም ጉዳዮች በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ተጠንቶ መፍትሄ እስከሚደረግበት ባለበት ቆመው ይቆያሉ፣
4. ለዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 አፈፃፀም የተገለፀው ጥናት በስድስት ወር ውስጥ መካሄድ አለበት፣

ዝተጠቐሰ ግዜ እንተዘይተወድኤን ዘይተወደአሉ ብቑዕ ምኽንያት እንተሃልዩን ቤት ምኽሪ ፈፃሚ ስራሕ ግዚያዊ ምምሕዳር ክናውሖ ይኽእል፣

5. ቅድሚ ሕዳር 30/2015 ዓ/ም ኣብ ዘሎ ግዜ መሰረት ዝገበሩ ኣብ ልዕሊ ክልልን ምምሕዳርን ዝቐርቡ ሕቶታት ይከፈለኒ ዝምልከት ሓዱሽ ዋኒን ክሲ ምትእንጋድ ተኣጊዱ ይፀንሕ። ብተመሳሳሊ ኣብ ከይዲ ክሲ፣ ይግባእን ኣፈፃፅማን ዝርከቡ ዋኒናት ክሳብ ዝምልከቶም ኣካላት መንግስቲ ተፀኒዑ መፍትሒ ዝገበረሉ ኣብ ዘለውዎ ደው ኢሎም ይፀንሑ፣

6. ካብ 24 ጥቅምቲ 2013 ዓ/ም ክሳብ እዚ ደንቢ ዝወፅእ ኣብ ትግራይ ወፂኦም ይስርሕሉ ብዝነበሩ ሕግታት፣ ውሳኔታትን ትእዛዛትን ናይ መወዳእታ ውሳነ ወይ ዕልባት ዝረኸበ ዋኒን ቅቡልነትን ሕጋውነትን ይህልዎ፤

7. ካብ 24 ጥቅምቲ 2013 ዓ/ም ክሳብ እዚ ደንቢ ዝፀድቕ እዋን ዘሎ እዋን ይርጋዕ ኣይቑፀርን፣

8. ድንጋገ ንኡስ ዓንቀፅ 3 እዚ ዓንቀፅ ከምዘለዎ ኮይኑ እዋን ይርጋዕ ምቑፃር ዝጀመረ ቅድሚ 24 ጥቅምቲ 2013 ዓ/ም ኮይኑ እዋን

በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካላለቀና ያላለቀበት በቂ ምክንያት ካለ የጊዜያዊ አስተዳደሩ ስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት ሊያራዝመው ይችላል።

5. ከህዳር 30/2015 ዓ/ም ያለ በፊት ባለው ጊዜ መሰረት ያደረገ በክልሉ እና አስተዳደሩ ላይ የሚቀርቡ የይከፈለኝ ጥያቄዎች የሚመለከት አዲስ የክስ ጉዳይ ታግዶ ይቆያል። በተመሳሳይ በሂደት ላይ ያሉ ክስ፣ ይግባኝና አፈፃፀም ጉዳዮች በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ተጠንቶ መፍትሄ እስከሚደረግበት ባለበት ቆመው ይቆያሉ፣

6. ይህ ደንብ እስኪወጣ ድረስ በትግራይ ውስጥ ወጥተው ይሰራባቸው በነበሩ ህጎች፣ ውሳኔዎች እና ትእዛዞች የመጨረሻ ውሳኔ ወይም እልባት ያገኘ ጉዳይ ቅቡልነት እና ህጋዊነት ይኖረዋል፤

7. ከጥቅምት 24/2014 ዓ/ም ይህ ደንብ እስኪጸድቅ ድረስ ባለው ጊዜ የይርጋ ጊዜ አይቆጠርም፤

8. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይርጋ መቁጠር የጀመረው ከጥቅምት 24/2014 ዓ/ም በፊት ሆኖ የይርጋ ጊዜው ከጥቅምት 24/2013 ዓ/ም በኋላ የሚያበቃ ከሆነ

ደርጊ ዝወጸኦ ድሕሪ 24 መጋቢት 2013 ዓ/ም እንተኸይዱ እዋን ደርጊ እዚ ደንቢ ካብ ዝወጸሉ እዋን ክሳብ ሓዲሽ ምትግባር ይጀምር።

9. ኣብ ትሕቲ ጊዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ኣብ ዘይኣተወ ዝኾነ ቦታ ትግራይ ንዝለዓሉ ዋኒን ገበን ከባቢያዊ ስልጣን ቤት ፍርዲ ብዝምልከት ኣብ ትሕቲ ዝኾነ ቦታ ጊዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ዝርከብ ብሰፈረ ሕጊ ስልጣን ዳኝነት ዘለዎ ቤት ፍርዲ ዝርኣዮ ይኸውን።

Criminal jurisdiction is amended for territories under occupation?

? ዓንቀጽ 9 ?

10. ንኣፈጻጽማ ንኡስ ዓንቀጽ 5 እዚ ዓንቀጽ ብመደበኛ ሕጊ ስልጣን ዝተወሃቦ ፖሊስን ዓቃቢ ሕግን ትግራይ ብቕደም ሰዓብ ዋኒን ገበን የጻሪ ክሲ የቕርብን።

ዓንቀጽ 12. ዝተሰዓረ ሕጊ

1. ኣዋጃት ህፁፅ እዋን፣ ደንብታት ህፁፅ እዋንን ንኢኦም መሰረት ገይሮም ዝወጹ መምርሒታትን ድንጋጌታትን ብዚ ደንቢ ተሳሒሮም ኣለዉ።
2. ነዚ ደንቢ ዝቃረን ዝኾነ ዓይነት ሕጊ ልምዳዊ ኣሰራርሓን ኣብዚ ደንቢ ኣብ ዝተሸፈነ ጉዳያት ተፈጻሚነት የብሉን።

የደርጉ ጊዜው ያለ ደንብ ከጸደቀበት ጊዜ እንደ አዲስ መተግበር ይጀምራል።

9. በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ስር ባልገባ ማንኛውም የትግራይ ቦታ ውስጥ ለሚነሳ የወንጀል ጉዳይ የፍርድ ቤት የአከባቢ ስልጣን የሚመለከት በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ስር ባለ ማንኛውም ቦታ የሚገኝ በመደበኛ ህግ የዳኝነት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የሚታየው ይሆናል።

10. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 አፈጻጸም በመደበኛ ህግ ስልጣን የተሰጠው የትግራይ ፖሊስ እና ዓቃቤ ህግ በቅደም ተከተል የወንጀል ጉዳይ ያጣራል ክስ ያቀርባል።

አንቀጽ 12. የተሻሩ ህግ

1. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች፣ ደንቦችና እነዚህ መሰረት አድርገው የወጡ መመሪያዎችና ድንጋጌዎች በዚ ደንብ ተሽረዋል።
2. ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ህግ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የለውም።

Scanned with AnyScanner

ዓንቀፅ 13. ስልጣን ምውፃእ መምርሒ

ቢሮ ፍትሒ ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ ነዚ ደንቢ መፈፀሚ ዝኸውን መምርሒ ከውፅእ ይኽእል።

ዓንቀፅ 14. ተፈፃምነት እዚ ደንቢ

እዚ ደንቢ ካብ ዕለት 26/[illegible]/2016 ዓ/ም ጀሚሩ ተፈፃምነት ይህልዎ።

ጌታቸው ረዳ

ርእሰ ምምሕዳር ግዚያዊ ምምሕዳር ክልል ትግራይ

መቐለ

አንቀጽ 13. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ለዚህ ደንብ የሚያስፈፅም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 14. የዚህ ደንብ ተፈጻሚነት

ይህ ደንብ ከ ቀን 26/[illegible]/2016 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

ጌታቸው ረዳ

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ርእሰ መስተዳድር

መቐለ





Scanned with AnyScanner